DHHS MONTGOMERY COUNTY
Department of Health and Human Services

# የግል መረጃ አጠባበቅ አሰራር ማሳወቂያ

**ይህ ማሳወቂያ የእርስዎ የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ እና እንደሚጋሩ ብሎም እርስዎ ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎ ይህንን በጥንቃቄ ያንብቡ ።**

## አገልግሎቶቻችን እና የምንሰበስበው መረጃ

የሞንትጎሜሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች ቢሮ (ዲኤችኤችኤስ) ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚሰጥ ትልቅ ተቋም ሲሆን የሚሰጣቸው አገልግሎቶችም የጤና፣ የአእምሮ ጤና፣ የአደንዛዥ እጽ፣ የልጅ ደህንነት የገቢ ድጋፍ እና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ናቸው። የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች ለእርስዎ አገልግሎቶችን ለመስጠት እንዲችሉ በመዝገብዎ ውስጥ የሚቀመጡ የግል መረጃዎችን ይጠይቁዎታል። ይህ መረጃ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

- እንደ ስምዎ፣ አድራሻዎ፣ ስልክ ቁጥርዎ፣ የትውልድ ቀንዎ እና የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥርዎ ያሉ የእርስዎን ማንነት የሚያረጋግጡ መረጃዎች።
- የገንዘብ መረጃ፤ ይህ መረጃ የሚያካታትተው ገቢዎን፣ የባንክ አካውንቶችን ወይም ሌላ ንብረት እንዲሁም ማናቸውንም ያሉዎትን ኢንሹራንስ ሽፋንን ነው።
- በምስጢር የሚያዝ የጤና መረጃ፣ ይህም ስለ አለፈው፣ ስለ አሁኑ ወይም ስለወደፊቱ የጤና ወይም አእምሮ ጤና ህክምና የሚያስረዳ ማናቸውንም መረጃ ይጨምራል።
- ስለሚያገኙዋቸው ወይም ከዚህ በፊት ስላገኝዋቸው ጥቅማ ጥቅሞች ወይም አገልግሎቶች መረጃ።

## የእኛ ኃላፊነቶች

የፌዴራል እና የስቴት ህጎች የእርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች በሚስጥር ይጠብቃሉ እኛም እነዚህን ህጎች አክብረን እንከተላለን። የመረጃዎን ደህንነት ጠብቀን ለማስቀመጥ ተገቢ እርምጃዎችን እንወስዳለን፣ መረጃዎን እንጠቀምበታለን (በዲኤችኤችኤስ ውስጥ እናጋራለን) እናም ለሌላም ዲኤችኤችኤስ ውጪ ለሆነም አካላት እንጠቀምበታለን(ከዲኤችኤችኤስ ውጭ ላሉ አካላት እናጋራለን)። ይህንንም የምናደርገው ስራችንን ለማከናወን አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ እና በህግ በሚፈቅደው ወይም በሚያዘው መሰረት ብቻ ይሆናል። የጤና መረጃዎን በተመለከተ በሚስጥር የመያዝ ስርአትን ወይም ደህንነትን የሚጥስ ነገር ከተፈጠረ ስለ ጉዳዩ ለእርስዎ ማሳወቅ ይጠበቅብናል።
ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በስተቀር በሌላ ምክኒያት የእርስዎን መረጃ መጠቀም ወይም ለሌላ ለማጋራት ካስፈለገን እርስዎን የጽሁፍ ፈቃድ እንጠይቃለን። የሰጡንን ማንኛውንም የጽሁፍ ፈቃድ የመሰረዝ መብት አልዎት። የሰጡትን ፈቃድ ከሰረዙ፣ ከዚህ በፊት የሰጡንን ፈቃድ መሰረት በማድረግ የተከናወኑ የመረጃዎን አጠቃቀምን ወይም ማጋራትን አይመለከትም።

መረጃዎን እንዲቀበሉ ወይም እንዲጠቀሙ የፈቀዱላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ለፌዴራል ወይም የስቴት መረጃን በሚስጥር የመያዝ ህጎች ተገገዢ ካልሆኑ፣ መረጃው ምንም አይነት ጥበቃ ላይደረግለት የሚችል ሲሆን መረጃውም ሊወጣ ይችላል።

ይህንን የግል መረጃን በምስጢር የመያዝ አሰራር ከዚህ ማሳወቂያ ጋር አንድ ላይ እንድንሰጥዎ እና ተግባራዊ እንድናደርግ ህግ ያስገድደናል። የዚህን ማሳወቂያ አንቀጾች መለወጥ እንችላለን፣ ይህም ለውጥ እኛ ጋር ባለዎት የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች ላይ ሁሉ ተፈጻሚ ይሆናል። አዲሱን/የተሻሻለውን ማሳወቂያ ማግኘት በሚፈልጉበት ጊዜ በቢሮአችን ማግኘት ይችላሉ፣ በተጨማሪም በዲኤችኤችኤስ ድህረገፅ ላይ ይገኛል ።
www.montgomerycountymd.gov/hhshttp://www.montgomerycountymd.gov/hhs

## የእርስዎን መረጃ እንዴት እንደምንጠቀም እና እንደምናጋራ

- **ለህክምና እና ለአገልግሎት፡-**

ከእርስዎ ጋር የሚሰሩ የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች ለእርስዎ የተቀናጀ ህክምና እና አገልግሎቶች ለመስጠት እንዲችሉ የእርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎች ይጠቀሙባቸው ይሆናል። የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች እርስዎ የሚያስፈልግዎትን ህክምና እና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ቴሌሄልዝ (telehealth)ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ቴሌሄልዝ (telehealth) ምንድን ነው ?
ቴሌሄልዝ (ወይም ቴሌ ሚድስን)/Telehealth (or telemedicine) የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች እንደ ስልክዎ፣ ኮምፒውተርዎ ወይም ታብሌቶዎ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከታካሚዎች ጋር የሚገናኙበት መንገድ ነው። ቴሌሄልዝ ድምጽ ንግግርን እንዲሁም በአብዛኛው ጊዜ ግን ቪዲዮን በመጠቀም እርስዎ እና የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ መነጋገር እንድትችሉ ይጠቅማል።

**<u>የቴሌሄልዝ</u>**
ጥቅሞች፣ አገልግሎት ወይም ህክምና ለማግኘት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎ ቢሮ በአካል መገኘት አይኖርብዎትም። ወደ ቀጠርዎ ቦታ ለመጓዝ ተጨማሪ ጊዜ ማባከን አያስፈልጎትም።

**<u>ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት፣</u>**
መረጃ ሊሰርቁ የሚችሉ ሀከሮችን (hackers) ለመከላከል እና የቴሌሄልዝ ቀጠሮዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ዲኤችኤችኤስ እርምጃዎችን ወስዷል። ዲኤችኤችኤስ በማንኛውም ምክንያት የእርስዎን የቴሌሄልዝ ቀጠሮ ውይይቶች ሪከርድ አያደርግም (አይቀዳም)።

ዲኤችኤችኤስ መከላከል የማይችላቸው አንዳንድ አደጋዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ዲኤችኤችኤስ የሚከተሉትን መከላከል አይችልም፡-
- በአካል አጠግብዎ ያሉ ግለሰቦች የእርስዎን ንግግር እንዳያዳምጡ ማድረግ።
- የእርስዎን የኢንተርኔት ኮኔክሽን የሚቆጣጠሩ ሰዎች የእርስዎን ኮኔክሽ ከማቋረጥ ወይም ንግግርዎን ከማዳመጥ።

ይህን አደጋ ለመቀነስ እንዲቻል፣የቴሌሄልዝ ቀጠሮዎ ላይ ሲሳተፉ የሚያምኑትን ወይም ደህንነቱ የተጠበቀ የኢንተርነት ኮኔክሽን መጠቀምዎን ያረጋግጡ። እንዲሁም ማንም ሊሰማዎ በማይችልበት የተከለለ ቦታ ላይ መሆንዎን ያረጋግጡ።

ዲኤችኤችኤስ የጤና ነክ እና ሌሎች የግል መረጃዎችዎን ለማስቀመጥ የተቀናጀ የጉዳይ አስተዳደር (integrated case management) እና የኤሌክትሮኒክስ የጤና ሪከርድ አሰራርን (electronic health record) ተግባራዊ አድርጓል። ከአሁን በፊት አገልግሎት ካገኙባቸው የጤና አገልግሎት ሰጪዎች፣የህክምና ምርመራ ካደረጉባችው ሌሎች የጤና ጥበቃ ተቋሞች፣ የጤና ኢንሹራንስ እንዲሁም እርስዎን ከሚንከባከብዎ የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ መረጃዎችን ልንሰበስብ እንችላለን። ከእርስዎ የህክምና መረጃ ውስጥ የተወሰነው ወይም ሙሉው በኤሌክትሮኒክ ፎርማት (electronic format) መልክ ሊዘጋጅ ወይም/እና ሊቀመጥ ይችላል።
ምሳሌዎች፡-

- ከክሊኒኮቻችን ውስጥ ባንዱ የጤና እንክብካቤ የሚያገኙ ከሆነ እና ለሌላ አገልግሎት ማለትም መኖሪያ ቤት እገዛ ወይም የገቢ ድጋፍ ለማግኘት ለማመልከት ከፈለጉ፣ የእርስዎን ጉዳይ የያዙት ሰራተኛ ወደ ሌላ አገልግሎቶች ሪፈር ሊያደርጎት እና የፕሮግራም ብቁነት መረጃዎን በማጋራት እነዚህን አገልግሎቶች እንዲያገኙ ሊያግዝዎ ይችላሉ።

- ከአንድ በላይ የዲኤችኤችኤስ አገልግሎት የሚያገኙ ከሆነ፣ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ወጥ የሆነ የአገልግሎት የአሰጣጥን ዕቅድ ለማውጣት እንዲቻል የእርስዎን ጉዳይ የያዙት ሰራተኞች እርስ በርሳቸው ብሎም ከእርስዎ ጋር ሊነጋገሩ ይቻላሉ።

ለተገቢው አላማ ሲፈለግ (ለምሳሌ፣ ህክምና እንዲያገኙ ወይም ለአገልግሎት ክፍያ በተመለከተ) የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች የጤና መጃዎን በኤሌክትሮኒክስ መልክ ሊያገኙ ይችላሉ። ሌሎች ለእርስዎ ህክምና የሚሰጡ ከዲኤችኤችኤስ ውጪ ያሉ የጤና አገልግሎት ሰጪዎች የኤሌክትሮኒክ መረጃዎን ሊያገኙ ይችላሉ።

የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች የእርስዎን የህክምና እና የአገልግሎት መረጃን በተመለከተ ከዲኤችኤችኤስ ውጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር የሚያጋሩት በእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ወይም በፌዴራል ወይም በስቴት ህግ በተፈቀደው መሰረት ብቻ ይሆናል። ለምሳሌ፣ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት እየሰጥዎት ያሉ የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች፣ ከዲኤችኤችኤስ ውጭ ላሉ እና ህክምና እየሰጥዎት ላሉ የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች የእስዎን የጤና መረጃ እንዲያጋሩ የፌዴራል እና የስቴት ህግ ይፈቅዳል።

**<u>የስነ ባህሪ ጤና (behavioral health) አገልግሎቶችን ከእኛ የሚያኙ ከሆነ ፡-</u>**
- የአእምሮ ጤና መረጃዎን ለእርስዎ ህክምና ወይም አገልግሎት ለማቅረብ ሲባል ያለ እርስዎ ፈቃድ ልናጋራ እንችላለን፤ የምናጋራው ግን ህክምናዎን ወይም አገልግሎቶን የሚመለከት መረጃ ብቻ ይሆናል።

- የጤና እንክብካቤ ሰጪዎቻችን በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎች እንዲያደርጉ እና የጤና እንክብካቤዎን እንዲያስተባብሩ የእርስዎን የጤና እና የስነ ባህሪ ጤና(health and behavioral health information ) መረጃ በአንድ የኤሌክትሮኒክ የጤና ሪከርድ ውስጥ እንይዛለን።
- በአብዛኛው የሳይኮቴራፒ ሕክምና መረጃዎችን (psychotherapy notes) የምናጋራው በእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ብቻ ነው። ሳይኮቴራፒ ሕክምና ጽሁፎች (Psychotherapy notes) በህግ እንደተደነገገው መሰረት በአእምሮ ጤና ሀኪም ተዘጋጅተው ከጤና ፋይልዎ ተለይተው የሚቀመጡ ናቸው። በአጠቃላይ፣ሰራተኞቻችን ሁሉንም የሕክምና መረጃዎችን በጤና ፋይልዎ ላይ የሳይኮቴራፒ ሕክምና ጽሁፎችዎን ጨምሮ ሳይለዩ አንድ ላይ ያስቀምጣሉ።
- የአልኮል ወይም የአደንዛዥ እጽ መጠቀምን በተመለከተ የእርስዎን ፋይሎች እርስዎ የሚከተሉትን ካላደረጉ በስተቀር አናጋራም:-
    - የጽሁፍ ፍቃድ ሲሰጡን፣
    - ይፋ ማድረጉ በየፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተፈቅዶለታል (ሪከርዶች ወይም ስለያዙት መረጃ ምስክርነት መስጠት ያለእርስዎ ስምምነት ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በህጋዊ ሂደቶች ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም)።
    - መረጃው በድንገተኛ ህክምና ላይ ያሉ የህክምና ባለሙያዎች ወይም ለተመረጡ ባለሙያዎች ለጥናት፣ቁጥጥር ወይም የፕሮግራም ግምገማ ጥቅም ላይ እንዲውል ሲጋራ፤
    - የእርስዎን መረጃ በተመለከተ ከእኛ ጋር መረጃውን በጥንቃቄ መጠበቅን በተመለከት ስምምነት ካደረገ የእርስዎ ህክምና ወይም የህክምና አገልግሎት አቅራቢ ጋር ስናጋራ፤ *እነዚህ ስምምነቶች የእርስዎን አደንዛዥ እጽ መጠቀምን በተመለከተ ያሉ ፋይሎችን ከዲኤችኤችኤስ የጤና እና አእምሮ ጤና አገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ለማጋራት የሚያስችሉ ናቸው።*
- በህግ ከተደነገገው ሁኔታ በስተቀር ጥቃት ከደረሰባቸው ሰዎች፣ የተጎጂዎች እርዳታ እና የወሲብ ጥቃት መከላከል ፕሮግራሞች ጋር መረጃዎችን ከእርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ውጪ አናጋራም። እነኚህ ፕሮግራሞች በእኛ የኤሌክትሮኒክ ሲስተም ውስጥ ብቻ ተወስነው የሚቀመጡ ናቸው።

**ከሥነ ተዋልዶ ሥርዓት፣ ተግባሮቹ እና ሂደቶች (የሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶች) ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ጤናዎን የሚነኩ አገልግሎቶችን ከተቀበሉ :-**

- ዲኤችኤችኤስ የእርስዎን ደህንነቱ የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI)በሚከተሉት ምክኒያቶች መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ አይችልም:-
    - የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI) እንደዚህ አይነት የጤና እንክብካቤ በሚሰጥበት ሁኔታ ህጋዊ የሆነ የስነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤን የሚፈልግ፣ ያገኘ፣ የሚያቀርብ ወይም የሚያመቻች ማንኛውንም ሰው ለመመርመር ወይም ተጠያቂ ለማድረግ በሚፈልግበት ጊዜ።
    - የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI) እንክብካቤን የሚፈልጉ ፣ ያገኙ፣ ያቀረቡ ሰዎችን ለመለየት ወይም ህጋዊ በሆነ መልኩ የሚከናወኑ የስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ለማመቻቸት በሚፈልግበት ጊዜ።
- ማንኛውም ሰው የስነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት መረጃን ለማግኘት ከጠየቀ መስማማቱን የሚያሳይ የተፈረመ ማረጋገጫ ለዲኤችኤችኤስ ማቅረብ አለበት። የተፈረመ ማረጋገጫ ግልጽ ማድረግ ያለበት ጉዳይ:-
    - የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI) ህጋዊ የሆነ የስነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤን የሚፈልግ፣ የሚያገኝ፣ የሚያቀርብ ወይም የሚያመቻች ማንኛውንም ሰው ለመመርመር ወይም ተጠያቂ ለማድረግ እንደማይፈልግ።
    - የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI) ህጋዊ የሆነ የስነ ተዋልዶ ጤና እንክብካቤን የሚፈልግ፣ የሚያገኝ፣ የሚያቀርብ ወይም የሚያመቻች ማንኛውንም ሰው ለይቶ ለማወቅ እንደማይፈልግ።
- ማረጋገጫ የሚያስፈልገው የአጠቃቀም ወይም መረጃን ይፋ ማድረግ ምሳሌ:-
    - ማንኛውም ሰው ስለ እርስዎ ከሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎት በተመለከት ከመፈለግ፣ ከመክፈል ወይም ከመቀበል ጋር የተያያዘ መረጃ ሲጠይቅ። ይህ አገልግሎቶቹን ከኛ ቢያገኙም ባያገኙም ተግባራዊ ይሆናል።

አንዳንድ ፕሮግራሞቻችን እንደ "የትምህርት ፋይሎች" የሚቆጠሩ መረጃዎችን በ 1974 የቤተሰብ ትምህርት መብቶች እና መረጃን በሚስጥር የመያዝ ህግ (FERPA) መሰረት ይይዛሉ። እነዚህን የእርስዎን ፋይሎች ከርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ውጭ ለድንገተኛ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ለሌላ አገልግሎት አቅራቢዎች አናጋራም።

ዲኤችኤችኤስ በቼሲፒክ ክልላዊ የታካሚዎች መረጃ ሲስተም(Chesapeake Regional Information System for Patients, Inc. (CRISP)) ውስጥ ለመሳተፍ መርጧል፣ ይህም ክልላዊ የመረጃ ልውውጥ አሰራር (regional health information exchange (HIE)) ነው። በህግ እንደተፈቀደው፣ የጤና መረጃዎ ከዚህ የመረጃ ልውውጥ ስርአት ጋር የሚጋራው አገልግሎት አቅራቢዎች እና የማሕበረሰብ ጤና ሰራተኞች ፈጣን የሆነ እና የተቀናጀ እንክብካቤ ለመስጠት እንዲያመቻቸው እና ተረድተው ውሳኔ ለማሳለፍ እንዲችሉ ያግዛል። በዚህ የመረጃ ልውውጥ ስርአት ውስጥ ላለመሳተፍ ከፈለጉ እና የጤና መረጃዎ በክሪስፕ (CRISP) ሲስተም ውስጥ ተፈልጎ እንዳይገኝ ከፈለጉ፣ ወደ 1-877-952-7477 በመደወል ወይም በፖስታ፣ በፋክስ ወይም ይህን ድህረ ገጽ www.crisphealth.org ተጠቅመው መውጣት የሚችሉበትን ቅጽ መሙላት ይችላሉ። በክሪስፒክ (CRISP) ሲስተም ውስጥ ከወጡ ፣ የጤና አግልግሎት አቅራቢዎችዎ ኤችአይኢን

(HIE) ተጠቅመው የላብራቶሪ ውጤትዎን፣ የራጅ ውጤትዎን እና ሌላ የሚላክላቸውን መረጃ በፋክስ ወይም በፖስታ ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክ መንገድ ያገኙትን ጨምሮ ማግኘት ይችላሉ። በህግ የተፈቀደ የማሕበረሰብ ጤና ሪፖርት ማለትም እንደ ተላላፊ በሽታ ያለ በማሕበረሰብ ጤና ሰራተኞች ጥቅም ላይ የሚውል ሪፖርት፣እርስዎ ከሲስተሙ ከወጡም በሁዋላም ይህ መረጃ በኤችአይኢ (HIE) በኩል ይተላለፋል።

**<u>የጤና መረጃ፡</u>** ስለ ሕክምና አማራጮች፣ ሌሎች አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማ ጥቅሞችን እና አገልግሎቶችን ለእርስዎ ለመስጠት እንዲቻል የእርስዎን የጤና መረጃ ልንጠቀም ወይም ልናጋራ እንችላለን።

**<u>የዲኤችኤችኤስ ዳሬክቶሪ(Directory)፡</u>** እርስዎ ካልተቃወሙ በስተቀር ስምዎን እና አጠቃላይ መረጃዎን የመሳሰሉ ጤና ነክ መረጃዎን ለዳይሬክቶሪ ልንጠቀም እንችላለን። በዳይሬክቶሪያችን ውስጥ የተካተተው መረጃ ከእኛ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ጋር ተዛማጅ ካልሆኑ ግለሰቦች ጋር በእርስዎ ፈቃድ እንዲጋራ አይደረግም።

- ***ለክፍያ፡-*** ለተደረገልዎ የጤና ወይም የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ክፍያ ለመቀበል እንደአስፈላጊነቱ የእርስዎን የጤና ወይም የግል መረጃ ልንጠቀምበት ወይም ለናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፡-ለተደረገልዎ ህክምና ከሜዲኬድ ወይም ከሜዲኬር (Medicaid or Medicare) ክፍያ ለመጠየቅ መረጃዎን እንጠቀም ይሆናል።

- ***ለጤና እንክብካቤ፣ የስራ እንቅስቃሴዎች፤*** የእኛን ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች ለማስተዳደር እንዲቻል የእርስዎን የጤና ወይም የግል መረጃ ልንጠቀምበት ወይም ለሌላ ልናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፣ በዲፓርትመንቱ በኩል የሚያገኙትን የአገልግሎት ጥራት ለመመርመር እንዲቻል የዲኤችኤችኤስ ሰራተኞች ወይም የውጭ ኦዲተሮች የአገልግሎት ፋይሎን ይመለከቱ ይሆናል።

- ***ለቀጠሮዎች ወይም ማሳወቂያዎች፡-*** ቀጠሮ ለመያዝ ወይም ስለ ቀጠሮ ለማስታወስ፣ የሚሞሉ ዶክመንቶችን ለማጠናቀቅ፣ ሊፈልጉዋቸው ስለሚችሉ ስለሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ለማሳወቅ ወይም በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እንድናገኝዎ ከእርስዎ ወይም ከተወካይዎ ጋር ልንገናኝ እንችላለን።

- ***የስራ ተባባሪዎቻችን፤፡-*** እንደ የገንዘብ ሂሳብ አስተዳደር ወይም የህግ አገልግሎቶች፣ የመረጃ ትንተና እና የአገልግሎት አሰጣጥ ፍቃድ እንዲሁም የአገልግሎት ጥራት ማረጋገጫ ምርመራን ያሉ የአስተዳደር እና የድጋፍ አገልግሎቶች ከሚያቀርቡ ከዲኤችኤችኤስ ውጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር ስምምነቶች አሉን። እነዚህ ሰዎች የስራ ተባባሪዎች ( business associates) ተብለው ይጠራሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ተግባራዊ ማድረግ እንዲችሉ ከስራ ተባባሪዎቻችን ጋር የእርስዎን መረጃ እናጋራ ይሆናል። ሆኖም የስራ ተባባሪዎቻችን የእርስዎን መረጃ በጥብቅ ምስጢር እንዲይዙ እናስገድዳለን።

- ***የእርስዎ ቤተሰብ፤ ጓደኞች እና በእርስዎ እንክብካቤ ውስጥ የሚሳተፉ ሌሎች አካላት፡-***የርስዎን መረጃ ለርስዎ ቤተሰብእና በርስዎ እንክብካቤ ውስጥ ለሚሳተፉ ሌሎች አካላት ልንገልጽ እንችላለን። ለምሳሌ፣ የቤት ውስጥ እንክብካቤን ከሚያደርጉልዎ ለአካለ መጠን ከደረሰ ወይም ከደረሰች ልጅዎ ጋር ስለ የህመምዎ ሁኔታ እንወያይ ይሆናል። ይህንን መረጃ ከቤተሰብዎ ጋር እንዳናጋራ ከፈለጉ፣ ይህን እንዳናደርግ ሊጠይቁ ይችላሉ። እርስዎ በጽሁፍ ፈቃድ ካልሰጡን በስተቀር ስለ አእምሮ ጤናዎ ወይም አደንዛዥ እጽን የመጠቀም ታሪክዎን ወይም በቤተሰብዎ ስለሚደረግልዎ እንክብካቤን በተመለከተ የእርስዎን መረጃ አናጋራም።

- ***ለመንግስት ፕሮግራሞች፡-***ለሌሎች የመንግስት ጥቅማ ጥቅሞች ወይም እንደ ሶሻል ሴኩሪቲ ጥቅማ ጥቅሞች ላሉ ፕሮግራሞ ብቁ መሆንዎን ለማጣራት እንዲቻል የእርስዎን የጤና እና ሌሎች የግል መረጃዎችን ልናጋራ እንችላለን።

- **ለህዝብ ጤና ጥበቃ ስራዎች፤** ለህዝብ ጤና ጥበቃ ተግባሮች የእርስዎን የጤና መረጃ እንጠቀምበት ወይም ለሌላ እናጋራ ይሆናል። ለምሳሌ፣ ለተላላፊ በሽታ ተጋልጠው ከሆነ (በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ) ይህን መረጃ ለስቴቱ እንገልጽ ይሆናል። እንዲሁም የዚህን በሽታ ስርጭት ለመከላከል ሌሎች እርምጃዎችንም እንወስድ ይሆናል።

- ***ለጤና ቁጥጥር ተግባሮች፤***ህጉ በሚጠይቀው መሰረት ፕሮግራማችንን ለኦዲት፣ ለምርመራ እና ፍቃድ ለመሳሰሉ የቁጥጥር ተግባር የሚያደርጉ ሌሎች መስሪያ ቤቶች የእርስዎን መረጃ ልናጋራ እንችላለን።

- ***ስለ ጥቃት እና የአያያዝ ጉድለት ሪፖርቶች እና ምርመራዎች፤*** በልጆች ላይ እና ተጋላጭ የሆኑ አዋቂዎችንም ጨምሮ፣እንደ ልጅ በደል የተፈጸመባቸው አዋቂዎች ጨምሮ የሚጠረጠሩ ጥቃቶችን እና የአያያዝ ጉድለቶችን ሪፖርት ማድረግ እና ማስታወቅ እንዳለብን ህግ ያስገድደናል። የጤና እና አእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጭዎች መረጃው ለምርመራ፣ ለአደጋ ተጋላጭነት ጥናት ወይም ለአገልግሎት ወይም ለደህንነት ፕላን ይጠቅማል ብለው ካሙኑ ለአዋቂ እና ህጻናት ጥበቃ አገልግሎት መረጃውን ሊያጋሩ ይችላሉ።

- **ጉዳትን ለማስወገድ፤**ዲኤችኤችኤስ በአንዳንድ ሁኔታዎች ስለ እርስዎ የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ ለህግ አስከባሪ አካል ይገልጽ ይሆናል። ለምሳሌ፥ ከሰራተኞቻችን መካከል ባንዱ ላይ ወይም በሌላ ተገልጋይ ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም በንብረታችን ላይ ጉዳት ካደረሱ ወይም የእኛ ባለሙያ ሰራተኞች እርስዎ በሌሎች ሰዎች ወይም በራስዎ ላይ ከባድ ጉዳት ያደርሳሉ ብለው ካመኑ፣ ለህግ አስከባሪ አካላት እናሳውቃለን። እንዲሁም ዲኤችኤችኤስ እንደ የአሸባሪ ጥቃት ወይም ድንገተኛ ከፍተኛ አደጋ ባጋጠመ ጊዜ የእርስዎን የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ ይገልጽ/ያጋራ ይሆናል።

- **ለሬሳ መርማሪዎች፣ የቀብር አስፈጻሚ ድርጅት ዲሬክተሮች፣ የሞት ምክንያት መርማሪዎች እና የአካል ክፍሎችን ልገሳን በተመለከተ** :-ዲኤችኤችኤስ ሞትን የሚመለከት የጤና መረጃ ለሬሳ መርማሪዎች፣የቀብር አስፈጻሚ ድርጅት ዲሬክተሮች እና እንዲሁም የአካል ክፍሎችን፣ ዓይን፣ ቲሹ (tissue) መለገስን ወይም ትራንስፕላንት (transplants) ማድረግን በተመከተ ለተፈቀደላቸው ድርጅቶች ይገልጽ/ያጋራ ይሆናል።

- **ለምርምር ተግባር:-** ባንዳንድ ሁኔታዎች ለህክምና ምርምር ጥናት የእርስዎን የጤና መረጃ እንጠቀምበት ወይም እንገልጽ ይሆናል።። ለአንዳንድ ጉዳዮች የርስዎ የጽሁፍ ፈቃድ ሊፈለግ ይችላል። የምርምር ጥናቶች እና ሪፖርቶች ግለሰቦችን በስም ለይተው አይገልጹም።

- **ለፍርድ ቤት ክርክሮች:-** በህግ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለፍርድ ቤቱ ስለርስዎ መረጃ እንድናቀርብ እንታዘዝ ይሆናል። ለሰራተኞች ካሳ ክሌም (workers' compensation claims) ሲባል የእርስዎን የጤና መረጃ እናጋራ ይሆናል።

- **ህግ በሚያዝዘው መሰረት:-** የእርስዎን የጤና ወይም ሌላ የግል መረጃ እንድንገልጽ ህግ ወይም ደንብ የሚያዘን ከሆነ ይህን መፈጸም አለብን።

- **ገንዘብ ማሰባሰብ:-**በአጠቃላይ ከደንበኞቻችን ጋር የገንዘብ ማሰባሰብ ስራ ላይ አንሳተፍም፣ ሆኖም ለገንዘብ ማሰባሰብ ጥረቶች ካነጋገርንዎ፣ በድጋሚ እንዳናናግርዎ ሊያሳውቁን ይችላሉ።

- **ከህልፈተ ህይወት በኋላ የጤና መረጃ አጠቃቀም።** ዲኤችኤችኤስ የእርስዎን የጤና መረጃዎች ህይወትዎ ካለፈ በኋላ እስከ ሃምሳ (50) አመት ድረስ ያለፈቃድዎ መጠቀም ወይም ይፋ ማድረግ ይችላል። ይህን የሚጋራ መረጃ የመገደብ መብት አለዎት።

## የእርስዎን መረጃ በተመለከተ ያሉዎት መብቶችዎ

**የሚከተሉት መብቶች አሉዎት:-**

- የዚህን ማሳወቂያ ኮፒ የማግኘት። ጥያቄ ሲቀርብ ይህን ማሳወቂያ በተለያየ ቅርጽ (format) ማግኘት ይቻላል።
- ሁልጊዜ ከምናገኝዎት ስፍራ ውጭ እንድናገኝዎ ወይም ሌላ ዘዴ በመጠቀም እርስዎ ጋር እንድንገናኝ እኛን የመጠየቅ። ለምሳሌ፣ እቤትዎ መጥተን ከመገናኘት ይልቅ በስልክ ወይም በደብዳቤ እንድንገናኝዎ የመጠየቅ።
- ስለ እርስዎ ያስቀመጥነውን መረጃ የማየት፣ የመመርመር እና ኮፒ የማግኘት። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎ፥* *መረጃዎን ኮፒ ለማድረግ ለሚያስፈልገው ወጭ ክፍያ እንዲፈጽሙ ሊጠይቁ ይችላሉ።* *መረጃዎን የመመርመር ወይም ኮፒ የማግኘት መብት ልንሰጥዎ የማንችልባቸው ሁኔታዎች አሉ።* ይህ ከተከሰተ፣ ለምን እንደሆነ እናስረዳለን። የእርስዎን የጤና መረጃ በኤሌክትሮኒክ ፋይል ውስጥ ካስቀመጥነው፣ መረጃዎን በኤሌክትሮኒክስ ፎርማት መጠየቅ ይችላሉ።
- ትክክል ያልሆነ ወይም ያልተሟላ ነው ብለው የሚያስቡትን መረጃዎን እንድናስተካክል ይጠይቁን። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎት።* በአንዳንድ ሁኔታዎች ለውጡን እንድናደርግ አንገደድም። ለውጡን ለማድረግ ካልተስማማን፣ ምክኒያቱ ምን እንደሆነ እንገልጻለን።
- ከጠየቁበት ጊዜ ጀምሮ ላለፉት ስድስት አመታት ድረስ ስላጋራነው እርስዎ መረጃ ዝርዝር ሪፖርት ማግኘት እንዲችሉ ይጠይቁ። ይህ ሪፖርት ለህክምና፣ ለክፍያ ወይም ለጤና እንክብካቤ ዓላማ እንዲውል በእርስዎ ፈቃድ ያጋራነውን መረጃ አይጨምርም። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎ።*
- የእርስዎን መረጃ ለእርስዎ ቤተሰብ እና ለሌሎች በርስዎ እንክብካቤ ለሚሳተፉ ሰዎች እንዳናጋራ ጥያቄ ማቅረብ።
- የጤና መረጃዎን ለህክምና እና አገልግሎት፥ ለክፍያ ወይም ጤና እንክብካቤ ተግባር ዓላማ እንዳንጠቀምበት ወይም ለሌላ እንዳንገልጽ ጥያቄ ማቅረብ። *ይህንን ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለብዎት።* የሚቀርቡትን ጥያቄዎች እድንፈጽም አንገደድም ነገር ግን ለእርስዎ ድንገተኛ አደጋ ህክምና መረጃውን መግለጽ ካላስፈለገን በስተቀር ስምምነቱን አክብረን መፈጸም አለብን። ጥያቄዎን ለመቀበል እና ለመፈጸም ካልቻልን ለምን እንደሆነ እንገልጻለን።
- ለአገልግሎት ወይም ለጤና እንክብካቤ ከኪስዎ ሙሉ ለሙሉ ከከፈሉ፣ ለክፍያ ወይም ከጤና ኢንሹራንስ አቅራቢዎ ጋር ላለን የስራ ግንኙነት መረጃውን እንዳናውለው መጠየቅ ይችላሉ። ህግ መረጃውን እንድናጋራ እስካልጠየቀን ድረስ የእርሶን ጥያቄ ለሟሟላት እንስማማለን።

- የእርስዎን መረጃ ለመሸጥ ወይም መረጃዎን ለማስታወቂያ ስራ ለማጋራት ከፈለግን የእርስዎን የጽሁፍ ፍቃድ እንድናገኝ መጠየቅ ይኖርብናል።
- መረጃዎ ለአደጋ ከተጋለጠ ይህን የሚገልጽ ማሳወቂያ ከእኛ ይደርስዎታል።
- መብትዎን የጣሰን መስሎ ከተሰማዎት የክስ አቤቱታ ማቅረብ ወይም ችግርዎን ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። የክስ አቤቱታ በማቅረብዎ አንዳችም እርምጃ በእርስዎ ላይ አንወስድም። የክስ አቤቱታ ለማቅረብ ወይም ችግርዎን ለመግለጽ እንዲችሉ የፕራይቬሲ ኦፊሰሩን (Privacy Officer) በሚስጥር በሚከተለው አድራሻ ያነጋግሩ።

  ፕራይቬሲ ኦፊሰር (Privacy Officer)
  የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት
  401 Hungerford Drive
  Rockville, MD 20850
  240-777-1295
  PrivacyMatters@montgomerycountymd.gov

  የክስ አቤቱታዎ ወይም ቅሬታዎ የእርስዎን *የጤና መረጃ* የሚመለከት ከሆነ፣ የሚከተለው ቢሮ ጋር በመደወል መነጋገር ይችላሉ። የዩኤሳኤስ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት (U.S. Department of Health and Human Services) የስልክ ቁጥር 1-877-696-6775.

## ጥያቄ እንዴት እንደሚቀርብ

ስለኛ የግል መረጃ በሚስጢር የመያዝ አሰራሮች ላይ ጥያቄ ካለዎ ወይም ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ማንኛውንም ከፈለጉ፣ ከርስዎ ጋር ከሚሰሩት ሰራተኛ ጋር ይገናኙ፤ ወይም በዚህ ማሳወቂያ መጨረሻ ላይ አድራሻቸው ከተዘረዘረው የእኛ መረጃን በሚስጥር የመያዝ አሰራር ሀላፊዎች (Privacy Official)ጋር ይገናኙ። በጽሁፍ መቅረብ ስላለባቸው ጥያቄዎች *የዲኤችኤችኤስ የደንበኞች ጥያቄ ማቅረቢያ ፎርም(DHHS Client Request Form)* እንዲጠቀሙ እንጠይቃለን። ጥያቄ ማቅረቢያውን ፎርም ከማናቸውም የዲኤችኤችኤስ ቢሮ ወይም የኛን የፕራይቬሲ ኦፊሰር (Privacy Officer)በመጠየቅ ማግኘት ይችላሉ።

*በስራ ላይ የሚውልበት ቀን፡- ይህ ማሳወቂያ ከኦክቶበር 30፣ 2024 ጀምሮ በስራ ላይ ይውላል።*